




Barack Obama – U.S. Senator for Illinois 2007

Martin Luther King (1964)

# ዕንቁ ቀለም በቀማኞች የትዕቢት ድንኳን ሲደበድብ ! ! !

*ሥርጉተ ሥላሴ*
*ነሐሴ 1 ቀን 2001 ዓ.ም.*

## *ዓለም እራሷ ሥነ ጥበብ ናት። የዓለም ሥነ ጥበብ ደግሞ ጥቁር ነው።*

ጥቁርነት ውስጠ ንጥር ወርቅ ነው። መሬት ተውባ፤ አምሮባት፤ ወግ ደርሶት የምትኖረው በጥቁር ነው። ***ጥቁርነት የጥበብ መሠረት ነው።*** **ጥቁርነት ለዓለም ውስጥነት ልዩ ጉባኤ ነው። የዓለም ድርሳን ብጡለ ቀለም ጥቁር ነው።**

ጥቁር የዓለም ጌጥ፤ ፈርጥ ነው። ጥቁር በምድር ባይኖር ዓለም በበለቅ ትምታ ነበር።
የፈጠራ ልዩ መክሊት የተሰጠው የጥቁር ማኅበረሰብ ድንቅ፤ ሁለገብ የሆነው የዕውቀት ዛለ ቅንብሩ ነው ዓለምን የኅብረ ዜማዊ ሞገስ እድትላበስ ያደረጋት።

ኢትዮጵያ ሀገራችንም የፀጋው ታዳሚ በመሆኗዋ፤ አልማዝ የሚያሰራጨውን ቀለሚን ወዳው እና ፈቅዳው፤ እሱነቱንም በከበረ ድርጊት ስታውጅ መኖሯ ይታወቃል። ኢትዮጵያ ሀገራችን በቀደመ አሰተሳሰብ የተገራች በመሆኗ በአፍሪካ ሀገሮች መሥራች ጉልላት ከመሆኗም አልፎ ጉልተ - ማዕከልም ናት። የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኮሚሽንም በዚህችው የተከበረች ብርሃናማ ሀገር ይገኛል።

ይህም ብቻ አይደለም በአፍሪካ ወላዊ አህጉራዊ እንቅስቃሴዎች፤ ታሪክ የሚዘክራቸው መሪዎችን፤ የሥነ ጥበብ፤ የምርምር፤ የደህንነት የሁለገብ ዕውቀት ባለቤት የሆኑ ልጆቿ ለአፍሪካ ህላዊ ነጻነት እና አብሮአዊ አንድነት በድሪጊት ያጌጠ ጸዳል ባለቤት ናቸው።
*ኢትዮጵያ ለአፍሪካ የመንፈስ ቀለበት ናት ! !*

**ስለሆነም ኢትዮጵያ ሀገራችን አህጉራዊ ድርሻዋን በተሟላ ተፈጥሯዊ ጨዋነት እና ሥነ ምግባር የተወጣችው በጥቁርነቷ የወስጥ ውስጥነት ሙሉ ዕምነት እንጂ ጥቁርነቷን ተፀይፋ አልነበረም።**

የልጆቿ የዜግነት ደም መለያ ጥቁርነት አሰከብሯት፣ አስወድዷት፣ ከፍ አድርጓት የኖረ እንጂ በጥቁር እናትነቷ የተወቀሰችበት፣ ያፈረችበት፣ የተዋረደችበት፣ ሆነ ጥቁርነትን ተላልፋ የተወቀሰችበት አንደም የታሪክ አጋጣሚ አልነበረም። ይህ እንግዲህ *የኢትዮጵያ ፍጹም የሆነ የትወፊቷ አሰኳል ነው።*

***ጥቁርነት፣*** **...** አክበሮተ - ደማቸው ኢትዮጵያዊ የሆነ የመላ ልጆቿ ሩህ ነባቢተ - ነፍሳቸው ነው። የማንነታቸው መግለጫ ***ዓርማችን*** ነው። የእኛነታችን መተርጎሚያ ***ባንዲራችን ነው*** መለያችን ነው። **ውቡ ጥቁርነት፣** ... ኢትዮጵያውያን በምንኖርበት በምንሰራበት፣ በምንማርበት አካባቢ ሁሉ እራሳችንን ገልጸንበት የኖርነው ***ረቂቅ ህዋሳዊ የከበረ ቅኔአዊ የውስጥነት ልዩ ሥነ ምግባር ነው።***

እንግዲህ ይህ የዞረባቸው ሜዳ በቀል የዘመን እሾኖች ህግ በመተላለፍ አልፈው ተርፈው የዓለምን መሪ በታሪክ ታይቶ በማይተወቅ ሁኔታ ከእጩ ውድድር እሰከ ፍፃሜው ድረስ በታላቅ ሥራዓት ከጅምሩ እሰከ ፍጻሜው በአተኩሮት፣ በተደሞ በአንክሮ በአጽህኖት የመረጣቸውን ***የመጀመሪያው ጥቁር አፍሪካዊ እና አሜሪካዊ ተወላጅ ፐሬዚዳንት ባራክ ኦባማን ኒገር ወይም ባሪያ በማለት ዘለፉ። የጥቁር ጠላት ዘረኞች...***
http://ecadforum.com/blog/2009/08/05/ethiopia-beyond-shame-the-madness-of-aiga-forum/
እኔ ፐሬዚዳንት ባራክ ኦባማን የአሜሪካ ሕዝብ ብቻ መረጣቸው ማለት አልችልም። መላ የዓለም ሕዝብ በታላቅ ተስፋ ነበር፣ በሙሉ ተሳትፎ የመረጣቸው። ይህ ታሪክ ከስንት መቶ ክፍለ ዘመን በፊትም አልነበርም፣ ወደፊትም በምን ያህል ዘመን ሊደገም
እንደሚችል መተንበይ አይቻልም።

ዓለም በአህቲ ስሜት እንደዚያ ሲፈነድቅ፣ ተቃቅፎ ሲሳሳም እንኳን ደስ አለን ሲባባል ሲጨፍር ነበር ያደረው። የዓለም ማናቸውም የሚዲያ አውታሮች ሁሉም ሙሉውን ኃይላቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ጊዜአቸውን፣ የህሊና ዕሴቶቻቸውን ሁሉ ያዋሉበት ልዩ ***ፍጹም ልዩ ሥነ ጥበባዊ ትዕይንት*** ነበረ። እያንዳንዳችንም በሕይወት እስካለን ድረስ ትዕይንቱ በህሊናችን በልዩ ሁኔታ የሚቀመጥ ሀብትም ነው።

*አዲስ የዓለም ምዕራፍ ተከፈተ። የዘመኑ ባህሪም ተለወጠ። አንድ አፈሪካዊ አሜሪካዊ ጥቁር ዓለምን ለመምራት ዓለም በሀሴት ስታስተናግድው ፐሬዚዳንት ባራክ ኦባማ የመጀመሪያው ቀንዲል ፋና ናቸው።*

ህሊናውም መንፈሱም ልቡም የታወረበት የአይጋ ፎረም ባሪያ ወይንም ኒገር ብሎ ሲጽፍ የዓለምን ድንቅ ፀሀይ ጨፈለቀ ከማለት ሌላ ከቶ ምን ሊባል ይችል ይሆን? ! ቋንቋ የራቃቸው አቶ ሀጎስ የዓለምን *ዕንቁ የጥቁር ቀለም በትዕቢት ድንኳናቸው ደበደቡት። በመዳፈር ህግን ተላልፈው ጠቀጠቁት። የዓለምን ህሊናዊ ብቃት በማናለብኝነት ፈረስ ረገጡት። የጥቁርነት ክብር በትምክት ሰጋር ጨቀጨቁት። ዘረኝነቱ ከሀገር አልፎ ዓለምን አካለለ።*

*በብዕራቸው ዘመን ይቅር የማይለው ጥላሸት ታሪክ እራሳቸውን አሰመጡ ! ለጎሰኝነት ሲሳመጡ አራሳቸም ሰመጡ ! የሥነ ጥበብን ግርማ አና ሞገሰንም ማቅ አለበሱት ! ብቻቸውን ቀሩ። አርቃነ መንፈሳቸውን ከትዕቢታቸው ጋር ተገትሮ መለመላውን ቀረ !*

የተከበራችሁ ወገኖቼ ፖለቲካዊ ትርፉን ለመመዘን ረቂቅ በመሆኑ አይቻለም እንጅ አስራ - ስምንት ዓመታት ደክምን ካገኘናቸው ዕሴቶች በላይ ነው ለእኔ። ስለሆነም የጥቁርነት ቀለም ቤተሰብ አገሮች ሁሉ በወያኔ ውስጥ ያለውን የትዕቢት ጋራ በሚገባ ይፈትሹ ዘንድ ልዩ ጥሪ ማደረግ የምንችልበት ወቅት አሁን ነው።
በእጃችን የተገኘው ሀብት ወያኔን የዓለም ጥቁር ሕዝብ ዓይኑ ከፈቶ እንዲያ- ስተውለው፣ ኢትዮጵያ በምን ዓይነት ጭፍን ጋጠ ወጥ አስተዳደር በመመራት ላይ እንዳለች ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ስለሆነ በየትኛውም ቦታ እና ሁኔታ ሳንታክት መልዕክቱን እናስተላልፍ።

መሠረቱ ሆነ የዘመቻው የእንቅስቃሴ ንቅናቄ የተመቸ ነው። ሰሞኑንን አዲሱ የአሜሪካ አስተዳደር ከተግባሮቹ ሁሉ የቅድሚያ ቅድሚያ በመስጠት ወደ ሰው ልጅ መገኛ፣ ወደ ዕንቁው ቀለም ፊቱን አዙሯል።

ኢትዮጵያ ሀገራችን በገማ ፋሽስታዊ የወይን አመራር እየታመሰች በመገኘቷ፣ ባይታወር መሆኗ ባለመታደላችን ቢያሳዝነንም፣ አዲሱ አስተዳድር የወሰደው እርምጃ ግን ይበል የሚያሰኝ ነው።

የኢትዮጵውያን ዕንባ ዋጋ አምርቷል። ስለሆነም የሰባት አፈሪካዊ ሀገሮች የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚ/ የክብርት ወ/ሮ ሂሌሪ ክሊንተን ጉብኝት ደጋፊ አካል መሆናችን ለመግለጽም ስልትም መቀየስ ያለበት ይመስለኛል። ዓለም ዓቀፋዊ ዕውቅና ለማግኘት ተደማጭነት የሚያሰገኙ ጉዳዮችን በአግባቡ ልንመራቸው ይገባል።

የቀማኞች የትዕቢት ድንኳን አፈ ጎባኤ አይጋ ፎረም አመለጠው። ውስጡ ቢፈታተሽ ከሚያሳየው በላይ እራሱን አጋለጠ። ተመሰገን! ኢትዮጵያ ያለችበትን ረገረጋዊ ሁነት ቁልጭ አድርጎ አሳዬ። ኢትያጵያን ያህል ታላቅ ሀገር በምን ዓይነት ሥርዓት አልበኛ
ዘረኛ ቡድን እየተመራች መሆኗንም ፍንተው አድረጎ አሳዬ። **ዘመነ ሂትለር በኢትጵያ።**

በሌላ በኩል በጥቁርነት ቀለማችን የሚጋሩት የማናቸውም ሀገር ሕዝቦች ትግሉን እንዲቀላቀሉ ማድረግ ሁለት ትርፍ አለው። አንዱ ድላችን አጋር ያገኛል። ሁለተኛው ደግሞ ከወያኔ ውድቀት በኋላም የጀርቱ አስተዳደር ሆነ አረግራጊዎች ጥግ አልቦሽ እንዲሆኑ ጊዜ በራሱ ዳኝነቱን ሰለጠ ከለላ አልቦሽ መሰናዶን ያሚላል። ዕውነት ምንጊዜም ዕውነት ነው መቼውንም።

ስለዚህም በየትኛው አጋጣሚ ከዓለም ዓቀፉ ድርጅት ከተባበሩት መንግስታት ጀምሮ በየሀገሩ ያሉ የሴቶች፣ የወጣቶች የጥቁር ማኅበረሰብ ድርጅቶች አፍሮ አፍሪካንስ፣ የጃማይካ ተፈሪያንስ ሁሉ ጉዳዩን አውቀው እንዲያወግዙት ጥረታችን መቀጠል አለብት።

ከዚህ ጋር ለዓለም ጋዜጠኞች ኀብረት እንዲሁም ስለ ሀገራችንም በቂ መረጃ ላለው የአፍሪካ ጋዜጠኞች ማህበር ማሰወቅ ጠቃሚ ነው። በተጨማሪም ለሲ.ኤን.ኤንም ..

በሌላ በኩል ደግሞ ጉዳዩ የሰባዊ መብት ረገጣም በመሆኑ ለዓለም አቀፉ የሰባዊ ድርጅት ማሰወቅ የተገባ ሲሆን፣ በግልም ለምናውቃቸው አፍሪካዊ ጓዶኞቻችን ማሰረዳትም ይገባል። የተሳትፎ አናሳ የለውም። በእጃችን ለገባው ወርቅ ተገቢውን አክብሮት እና አትኩሮት መሰጠት የሁላችንም ድርሻ ነው።

በመጨረሻ ...

*<u>የኢትዮጵያ ከረንት አፊርስ ዲስከሽን ፎረም አንበሶች ላደረጉት የላቀ የባለቤትነት፣ ስሜት ሆነ ላሳዩት የኃላፊት ትጋት የዘመናችን የአርበኝነት መዳሊያ ቀዳሚ ተመዝጋቢዎች ይሆኑ ዘንድ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖቼን እንዲያስቡበት በታላቅ ትህትና እና አክብሮት እገልጣለሁ።</u>*

ገድል ነው የሰሩት። *<u>ተግባሩ የድላችን ዋዜማ ሳይሆን በራሱ ድል ነው።</u>* <u>ንቃታቸው፣ ትጋታቸው፣ ፍጥነታቸው፣ ህብረታቸው፣ መቅደማቸው፣ ... እራሱ አንድ በሙሉ ሥነ -ምግባር ከሰለጠነ ከታነፀ ሕዝባዊ ሠራዊት ጀግና መሪ ብቻ የሚገኝ በመሆኑ ድህረ ገፃችን ለእነዚህ የድርጊት ጀግኖች ያለውን የላቀ አክብሮት እና አድናቆትም ይገልጣል።</u>

**ጀግና በሁሉም መስክ ይወለዳል !**
**ጥቁርነታችን መለያ ደማችን ክብራችን ነው !**
**ቀለማችን የእኛነታችን ዓርማችን፣ ሠንደቃችን ነው !**
**አፍሪካዊነታችን ኩራታችን፣ ሰናያችን ነው !**